# በጀርመን ከኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የተሰጠ መግለጫ

"እርስ በርሱ የሚለያይ ቤት አይቆምም" - ማቴ.፡ 12.25

-----------------------------------------

እኛ በጀርመን ሀገር የምንገኝ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ካህናት እና ምእመናን ሰሞኑን በቤተክርስቲያናችን ቅዱስ ሲኖዶስ ላይ የደረሰዉን ፈተና ከልዩ ልዩ ምንጮች በጥሞና ስንከታተል ነበር።

ስብከተ ወንጌል ተስፋፍቶ፣ የገጠር አብያተ ክርስቲያናት ችግር ተፈትቶ፣ ገዳማት እና አድባራት ከልመና ወጥተዉ እና በሚገባ ተደራጅተዉ፣ ካህናት እና ምእመናን የሚደሰቱበት ለሌሎች አርአያ የሚሆን አስተዳደር ተዘርግቶ ለማየት በነበረን ፍላጎት በየጊዜዉ እናት ቤተ ክርስቲያናችንን በምንችለዉ ሁሉ ስንደግፍ እና ከመንበረ ፓትርያርኩ የሚመጣዉንም ትዕዛዝ በዐቅማችን ስንፈጽም ቆይተናል።

ከሰሞኑ በቅዱስ ሲኖዶሳችን የተፈጠረዉ ችግርና ችግሩንም ለመፍታት የተፈጸሙት ተግባራት፣ ብሎም ሁኔታዉ ለሕዝብ የቀረበበት መንገድ ቤተ ክርስቲያናችን ምንም እንኳን በአንዳንድ ሁኔታዎች ዕድገት ብታስመዘግብም በብዙ ነገሮች ግን ከባድ ችግር ዉስጥ እንዳለች አስገንዝቦናል።

- ቅዱስ ሲኖዶስ ባነሣቸዉ ችግሮች ዙሪያ በነፃነት እና በመከባበር፣ ብሎም በሕገ ቤተ ክርስቲያን መሠረት ለመወያየት እና ለመፍታት አለመቻሉ፤
- ለሌሎች አርአያ ሆነዉ ችግሮችን በመንፈሳዊ እና አባታዊ መንገድ ይፈታሉ የተባሉ አባቶች ችግሩን በራሳቸዉ መፍታት አቅቷቸዉ የመንግሥትን ሽምግልና መጠየቃቸዉ፤
- ከቅዱስ ፓትሪያርኩ እስከ ብፁዓን አበዉ ድረስ ያሉ አባቶች ቀድሞ ያልተረቀቀ፣ ሊቃዉንት ያልመከሩበት፣ ግራ ቀኙ ያልታየ መግለጫ በየፊናቸዉ ሲሰጡ መስማት፣ ከዚሁ ጋራ ቤተ ክርስቲያኒቱን ያማከለ ቃል አቀባይ ያለመኖር፤ ችግሩ በተፈጠረ ጊዜ መግባባት እና ወደ አንድ ሃሳብ መምጣት ሳይቻል ሲቀር እንጸልይበት፣ ሱባኤ እንያዝበት ከማለት ይልቅ ሥልጣንን፣ ኃይልን እና ተሰሚነትን በመጠቀም ብቻ በመጓዝ የተስተዋለዉ ሁኔታ፤
- በቤተ ክርስቲያኒቱ ትምህርት ያልበሰሉ፣ የቤተ ክርስቲያኒቱ መዓረግም የሌላቸዉ ሰዎች ከችግሮቹ ጀርባ አሉ እየተባሉ በተደጋጋሚ ስማቸዉ መነሣቱ፤
- እንኳንስ በቤተ ክርስቲያን አባቶች፤ በዓለማዉያን ዘንድ እንኳን በማይፈጸም ሁኔታ የቤተ ክርስቲያኒቱ አስተዳደር ችግር እንዲፈታ ድምፃቸዉን አሰምተዋል የተባሉ አባቶች ቤት ከመጨረሻዉ ስብሰባ በፊት በመንበረ ፓትሪያርኩ ግቢ እና በዉጭ ባልታወቁ አካላት መደብደቡ፣ መሰበሩ እና የደረሰባቸዉ ማስፈራራት እና የሥነ ልቡና ተፅዕኖ
- ችግር አለ ብሎ የጮኸን አካል በማገድ እና ከሥራ በማንሣት የተወሰነዉ ዉሳኔ፤
- የብፁዓን አባቶችን ቅድስና፣ መንፈሳዊ አገልግሎት እና ታማኝነት አደጋ ዉስጥ በሚጥል መልኩ በብፁዕ አቡነ ሳሙኤል ላይ የወጣዉ አስጸያፊ እና አሳዛኝ መጽሐፍ፣ በዛሬዉ እና በመጭዉ ትዉልድ ላይ የሚያደርሰዉ ጉዳት እየታወቀ ድርጊቱ በተፈጸመ በሁለተኛዉ ቀን በወጣዉ በቅዱስ ሲኖዶሱ የመጨረሻ መግለጫ ላይ ድርጊቱም ሆነ አድራጊዎቹ ሳይወገዙ መታለፋቸዉ፤

እኛን በጀርመን ሀገር የምንገኝ ካህናት እና ምእመናንን በእጅጉ አሳዝኖናል። በመሆኑም ይህ የቤተ ክርስቲያን ችግር ለወደፊቱ በማይደገምበት ሁኔታ እንዲፈታ ባለን ቅን ፍላጎት እና በልጅነታችንም ጉዳዩ ስለሚመለከተን የሚከተሉትን ነገሮች

እንዲፈጸሙ በትጎትና አባቶቻችንን እናሳስባቸዋለን።

1. ቅዱስ ሲኖዶስ በቤተ ክርስቲያኒቱ መዋቅር የመጨረሻዉ ዉሳኔ ሰጭ አካል እንደመሆኑ አሁንም የተፈጠሩ ችግሮችን አስፈላጊዉን ጊዜ ወስዶ በመወያየት፣ በመከራከር እና በመተማመን በሕገ ቤተ ክርስቲያን መሠረት ያለ ማንም ጣልቃ ገብነት በራሱ እንዲፈታቸዉ፤
2. በምዕመናን እና በካህናት ከዚህ በፊት በተደጋጋሚ ሲቀርብ የነበረዉ የቤተ ክርስቲያኒቱ አስተዳደራዊ ችግር ዛሬ መፍትሔ ይሰጣል በሚባለዉ በቅዱስ ሲኖዶስ ደረጃም እየቀረበ መሆኑ አስተዳደራዊዉ ችግር ምን ያህል ሥር እንደሰደደ የሚያመለክት ነዉ። በመሆኑም ይህንን ለብዙ ዘመናት ከቀድሞ ጀምሮ እየተበላሸ የመጣ አስተዳደር በቤተ ክርስቲያኒቱ ሊቃዉንት አስጠንቶ፣ ምዕመናን፣ ካህናት እና የሚገባቸዉ አካላት ሁሉ ሃሳብ ሰጥተዉበት በቅዱስ ሲኖዶስ ጸድቆ ተግባራዊ እንዲደረግ፤
3. የመንበረ ፓትርያርኩን ጥበቃ እንዴት ሊያልፍ እንደቻለ ባልታወቀ ሁኔታ በብፁዓን አባቶች ቤት ላይ በመንበረ ፓትርያርኩ ግቢ፣ እንዲሁም ከመንበረ ፓትርያርኩ ዉጭ የተፈጸመዉ የዉንብድና ተግባር፤

   ሀ/ በማናቸዉም መልኩ በቤተ ክርስቲያን ሊታይም ሊሰማም የሚገባዉ ባለመሆኑ ቅዱስ ሲኖዶሱ እንዲያወግዝ
   ለ/ በሚመለከታቸዉ አካላት የድርጊቱ ፈጻሚዎች እና ተባባሪዎች ማንነት ተጣርቶ ለፍርድ እንዲቀርቡ፣ ለምእመናንም እንዲገለጥ፤

4. ችግሩን አዉጥተዋል በተባሉት አባት ላይ የተላለፈዉ እግድ ችግሩን የሚፈታ ሳይሆን የሚያድበሰብስ እና የሚያባብስ፣ ብሎም ሌሎችንም የሚያሸማቅቅ በመሆኑ እግዱ እንዲነሣ፣ ለወደፊቱም ይህ አካሄድ እንዳይደገም፤
5. ምዕመናን የቤተ ክርስቲያንን አባቶች መንፈሳዊ ሕይወት እንዲጠራጠሩ፣ መናፍቃንም መሳቂያ እና መሳለቂያ እንዲያደርጓቸዉ ዱላ የሚያቀብለዉ በብፁዕ አቡነ ሳሙኤል ላይ የተጻፈዉ መጽሐፍ እንዲወገዝ፣ የድርጊቱ አስተባባሪዎችም በሕግ እንዲጠየቁ፤
6. ምዕመናንም የአጵሎስ፤ የኬፋ ብለዉ ሳይለያዩ፣ ራሳቸዉን ከቡድን እና ከግለሰብ ድጋፍ ነፃ አድርገዉ፣ የቤተ ክርስቲያን ችግር ሊፈታ በሚችልበት መንገድ አስለፈላጊዉን አስተዋፅዖ እንዲያደርጉ እየጠየቅን፤

በመጨረሻም በጀርመን ሀገር የምንገኝ ካህናት እና ምእመናን ከፊታችን የሚመጣዉን ጾመ ፍልሰታ ስለ ቤተ ክርስቲያናችን እያሰብን ከልብ በመጾምና በመጸለይ እግዚአብሔርን ለመለመን መወሰናችንን በልጅነታችን ሃሳባችንን እናቀርባለን።

## እግዚአብሔር አምላክ ቤተ ክርስቲያናችንን እና ሀገራችንን ይባርክ!

---------

Äthiopisch-Orthodoxe Kirche in Deutschland
Erzpriester Dr. Merawi Tebege
Ückeratherstr. 2
50739 Köln

Tel./Fax:+49 221 5992623